# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 335 ጥቅምት 1 2007


ህወሃቶች አሁን ደርሰው የባንዲራ ተቆርቋሪ ለመሆን በቅተዋል። ባንዲራ ጨርቅ ነው ብለው የጨውና የበሶ መቋጠሪያ እንዳላደረጉት ሁሉ ዛሬ ደግሞ ብዙ ደም የፈሰሰላትን ባንዲራ አውርደው ጣሉ እያሉ እየተንጨረጨሩ ነው። ህወሃቶች አምስት ራስ ያለው ኮከብ ያስቀመጡበትን ባንዲራ ምልክታቸው ያደረጉት ያለ ምክንያት አይደለም። ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ ያለው ኮኮብ የዳዊት ኮከብ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎቹም ከአምባሻ ጋር አያይዘውታል። እኛ ከሁለቱም ጋር ቅራኔ የለንም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በረከት ስምኦን በእዉቀት የሚበልጡትን የዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች እያሰለጠነ ነዉ

ከአርከበ ዕቁባይ ኮሌጅ ዉጭ የዩኒቨርሲቲ በራፍ ዬት እንዳለ የማያዉቀዉና እሱ እራሱ ስልጠና የሚገባዉ በረከት ስምኦን አስተማሪዎቹን የዩኒቨርሲተ አስተማሪዎችን በማሰልጠን ላይ መሆኑን ከወደ አዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። በመላው አገሪቱ ለሚገኙ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ ለመንግስት ሰራተኞች እና ለያኔ/ኢህአዴግ አባላት የሚሰጠው የፖለቲካ ስልጠና የዩኒቨርስቲ መምህራንም እንዲወስዱ በመገደዳቸው፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን በቀድሞው የኮሚኒኬሽን ሚኒስትር እና በአሁኑ የጠ/ሚ የፖሊሲ አማካሪ በአቶ በረከት ስምኦን እንዲሰለጥኑ እየተደረገ ነው። ስልጠናውን የሚወስዱት በታሪክ፣ በፖለቲካል ሳይንስ፣ በሶሺኦሎጂ፣ በጆግራፊ፣ በፊዚክስ እና በመሳሰሉት የትምህርት ዘርፎች የፕሮፌሰርነት ማእረግ ያገኙ፣ የተለያዩ ጥናታዊ ምርምሮችን የሰሩና በሙያው የዶክትሬት ተማሪዎችን ሳይቀር የሚያስተምሩ ናቸው። ኢሳት ውይይቱን በርቀት በመከታተል ለመረዳት እንደቻለው አቶ በረከት በፌደራሊዝም፣ በታሪክ፣ በሃይማኖትና በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ዙሪያ ለአስተማሪዎች ስልጠና ሰጥተዋል። "ማለባበስ የማይቻለው የብሄረሰቦች ግጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ነው፣ ሚዲያው በወቅቱ ባይነግረንም ከተፈታ በኋላ 'ተፈጥሮ የነበረው ግጭት በሽማግሌ፣ በክልሉ የጸጥታ ሃይሎች፣ በፌደራል ፖሊስ፣ በመጨረሻም በመከላከያ ጥረት ሊፈታ ችሎአል' ይባላል።

በዚህ ከቀጠለ ግጭቶች በአለም ሰላም አስከባሪ ተፈታ ሊባይ ነው ወይ?" የሚል ጥያቄ አዘል አስተያየት ከአስተማሪዎች ተሰንዝሯል። አቶ በረከት በኢትዮጵያ ያለው የፌደራል ስርአት የብሄሮችን ጥያቄ የፈታ መሆኑን፣ ግጭቶች በአፈጻጸም የተነሳ አልፎ አልፎ እንደሚከሰቱ ተናግረዋል። የመገንጠል ጥያቄ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ቢቀመጥም እስካሁን ወደ ተግባር አልተለወጠም ያሉት አቶ በረከት፣ እስካሁን የመገንጠል ጥያቄ ያቀረበ ሃይል ባለመኖሩ ፈተና ውስጥ አለመግባታቸውን ተናግረዋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ "ጨርቅ" ብሎ የሰደበዉን ባንዲራ ለማክበር ጎንበስ ቀና እያለ ነዉ

የወያኔ ዘረኞች በረሃ እያሉ ዕቃ ይጠቀልሉበት የነበረዉንና አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ ደግሞ ጨርቅ ብለዉ ያሚረቱበትን የኢትዮጵያ ባንዲራ "የባንዲራ ቀን" በሚል ለማክበርና ይህንን ባዕድ አካል የለጠፉበትን ባንዲራ የኢትዮጵያ ህዝብ በግድ እንዲቀበልላቸዉ የሚያደርጉትን ጥረት አሁንም እንደቀጠሉበት መሆኑን ምንጮቻችን ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። በየአመቱ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ከሚፈስባቸው የወያኔ ክብረ በአላት መካከል አንዱ የሆነው የባንዲራ ቀን ዘንድሮም ጥቅምት 2 ቀን 2007 ዓም በአዲስአበባ ስታዲየም በድምቀት እንደሚከበር መንግስት አስታውቋል። "በሕዝቦች ተሳትፎና ትጋት ድህነትን ድል በመንሳት ብሔራዊ ክብሯን እና ሰንደቅ ዓላማዋን ከፍ ከፍ በማድረግ ላይ ያለች ሀገር!" በሚል መሪ ቃል ለ7ኛ ጊዜ በሚከበረው በዚህ በዓል ላይ ከአዲስአበባ ከተማ ከየወረዳው ሕዝቡ በተዘጋጀለት አውቶቡሶች ወደስታዲየም በማቅናት በደመቀ ሁኔታ በልማት የተገኙ ድሎችን በመዘከር ይከበራል ተብሏል። አቶ አባዱላ ገመዳ በቅርቡ በዓሉን አስመልክቶ በሰጡት መግለጫ የያዝነው በጀት ዓመት የትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን የሚጠናቀቅበት፣ በዕቅድ ክንውን ዘመኑ ሕዝብ ተጠቃሚ ያደረገ ሰፊ ተግባራት የተከናወኑበት በመሆኑ ይህን አጠናክሮ ለመቀጠል በዓሉ ቃል የሚገባበት እንደሆነ ተናግረዋል።

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት እንዲህ ዓይነት በዓላት ላይ ሕዝቡን ሥራ በማስፈታት ልማት፣ ሠላም፤ ዴሞክራሲ፤ ሕገመንግስታዊ ሥርዓት በሚሉ ኀሳቦችደጋግሞ በማንሳትና ራሱን ይበልጥ አማራጭ የለሽ ፓርቲ አድርጎ የሚያቀርብበት በተቃራኒው ደግሞ የሚቃናቀኑትን ኃይሎችደግሞ ሽብር ናፋቂዎችና ጸረሰላም ኃይሎች በማድረግ ፕሮፖጋንዳ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ የመከላከያ ሰራዊቱ ህብረብሄር ሆኗል ሲል ተመፃደቀ

የኢትዮጵያ ህዝብ መከለከያ ሠራዊቱን የወያኔ መከላከያ ሠራዊት ብሎ እስኪጠራዉ ድረስ ሠራዊቱን ከላይ እስከታች እንደቤት ዉስጥ ዕቃዉ የሚቆጣጠረዉ ወያኔ "የመከላከያ ሠራዊታችን ህብረበህራዊ ሆኗል ሲል መመጻደቁ ተሰማ። "የመከላከያ ሰራዊቱ ያዛዥነት ቦታዎች በአንድ ብሄር ቁጥጥር ስር ነው" በሚል ተደጋጋሚ ትችት የሚደርስበት ወያኔ፣ ሰራዊቱን ህብረብሄራዊ ማድረጉን የተናገረዉ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የድሞክራሲ ንቅናቄ የሠራዊቱ መሪነትና አዛዥነት ቦታዎች እንዳሉ በትግራይ ተወላጆች ቁጥጥር ስር መዉደቁን የሚያመለክት ጥናታዊ ሪፖርር ባወጣበት ሳምንት ነዉ። የተለያዩ የመንግስት ሰራተኞች እንዲወያዩበት ተብሎ በወያኔ/ኢህአዴግ የተዘጋጀው ሰነድ የትምክት ሃይሎች" በአገራችን የአንድ ብሄር የበላይነት ያለ ለማስመሰል የማያደርጉት ሙከራ የለም" ካለ በኋላ፣ ሰራዊታችን በህገ መንግስቱ መሰረት የተዋቀረ ህብረብሄራዊ ሰራዊት ሆኖ እያለና በመጀመሪያዎቹ አመታት ከትግሉ ጋር ተያይዞ የነበረውን አለመመጣጠን ረጅም ርቀት ተጉዘን እያለ ይህ እንዳልሆነ ለማስመሰል በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የማያቋርጥ የማጥላላት ዘመቻ ያካሂዱሉ" ብሏል። የትምክት ሃይሉ የሚኒስትርነት ሃላፊነትን እየቆጠረ ይህ ብሄር ከዚያኛው የበለጠ የደረሰው በማስመሰል ስርዓቱ የእኩልነት ሳይሆን የመበላለጥና መስሎ እንዲታይ ይጥራል ሲል ሰነዱ ያመለክታል። ኢህአዴግ የመከላከያ ሰራዊቱ ህብረብሄራዊ ሆኗል ቢልም ግንቦት 7 ከአራት አመት በፊት በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የነበረውን የብሄር ተዋጽኦ ያጠናበትን ሰነድ እንደገና ገምግሞ ሰሞኑን ይፋ ባደረገው ጥናታዊ ጽሁፍ፣ ተቋሙ ጭራሽ ከድጡ ወደማጡ እያዘገመ ነው ብሏል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የፕሬዚዳንቱን ሪፖርት ተቃወሙ

ፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመ መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክርቤቶች መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር በአዲስአበባ ባለፈው ዓመት 22ሺ ያህል የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለተጠቃሚዎች ተላልፈዋል የሚል ሪፖርት ማቅረባቸው ትክክል አለመሆኑን ገልጸዋል። ባለፈው ዓመት በሰኔ ወር በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት 22ሺ ያህል ቤቶች ቀደም ሲል ዕጣ ለወጣላቸው ሰዎች መተላለፉን አስተዳደሩ ይፋ ከማድረጉም በላይ አንዳንድ ግለሰቦች የቤቶቹን ቁልፍ ሲረከቡም በዕለቱ ታይተው ነበር።ነገር ግን 22ሺ የተባሉት ቤቶች ዕድለኞቹ በቴሌቭዥን ከማየታቸው በስተቀር አስካሁን ሊረከቡ እንዳልቻሉ አስረድተዋል። በየክፍለከተማው ቤቶች ማስተላለፊያ ጽ/ቤት ሄደው ሲጠይቁ «ገና ነው፤ ደውለን እንጠራችሁዋለን» የሚል ተመሳሳይ መልስ እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

የቤቶቹ ዕጣ ከደረሳቸው በኃላ በህዳር ወር 2006 ዓ.ም ከንግድ ባንክ ጋር የብድር ውል መፈጸማቸውን፣ በውሉ መሰረት ከአንድ ዓመት እፎይታ በሃሁላ የባንክ ዕዳ መክፈል ግዴታቸው መሆኑንና ቤቶቹን ተረክበው ከኪራይ ቤት ባልተላቀቁበት ሁኔታ ወደባንክ ዕዳ ክፍያ መሸጋገር እጅግ ከባድና የማይቻል በመሆኑ ሁኔታው እንዳሳሰባቸው ገልጸዋል።ፕሬዚደንት ሙላቱ ተሾመ የደረሳቸውን ሐሰተኛ ሪፖርት መሰረት አድርገው 22ሺ ቤቶች ተላልፈዋል ሲሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ መዋሸታቸው የአገዛዙን ይሉኝታ ያጣ ያልተገባ ባህርይ ያሳያል ብለዋል።በተያያዘ ዜና ፕሬዚደንት ሙላቱ ተሾመ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ችግር ለተፈጠረው ችግርና መስተጓጎል የኢትዮጵን ሕዝብ በነግግራቸው ይቅርታ መጠየቃቸው አግባብ ቢሆንም ኪሳራው ግን በይቅርታ ብቻ የሚታለፍ እንዳልሆነ ያነጋገርናቸው የአዲስአበባ ነዋሪዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ኤሌክትሪክ ኃይል ተርፎን ለጎረቤት ሀገር ጭምር ለመሸጥ ችለናል የሚል መንግስት አንዳንዴ በቀን ውስጥ እስከሶስት ጊዜ በተደጋጋሚ ኤሌክትሪክ መቆራረጥ እንደሚያጋጥም የገለጹት አስተያየት ሰጪ፣ አንድ ነዋሪ ይህ ደግሞየዜጎችን ገቢ ከመጉዳቱም ባሻገር እንደባንክ፣ ቴሌ፣ አየር መንገድ የመሳሰሉ ከኔትወርክና ኢንትርኔት ጋር የተያያዙ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ስራ የሚፈቱባቸው ጊዜያት እየተበራከቱ እንዲመጣ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል።

ይህ በተለይ እየተስፋፋ ነው በሚባለው የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳረፍ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ መካድ አይቻልም ሲሉ አስረድተዋል። "ባንክ ቤቶች ሄደህ ተመልከት" ሰዎች እንደዳበ ሰልፍ ቁጭ ብለው ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ጋጠ ወጡ ማን ነው ?

ከሰሞኑ በዋሺንግተን ዲሲ የህወሃት ኤምባሲ ውስጥ ከተፈፀመው ድርጊት ጋር ተያይዞ ብዙ ነገር ተብሏል። ለክስተቱ የተሰጠው ምላሽም የህወሃትን አራዊታዊ ባህሪይ ደህና አድርጎ አሳይቶ አልፏል። ህወሃቶች እንደ ሰው ልጅ ማሰብ አቅቷቸዋል። እንደ ሠው ለማሰብም ራሳቸውን የሚያዘጋጁ ቡድኖች ሊሆኑ አልቻሉም። ለኢትዮጵያችን ትልቅ ፈተና የሆነባትም ይሄ ከአራዊታዊ አስተሳሰብ ራሱን ለማላቀቅ ፍላጎት የሌለው ቡድን በአገሪቷና በህዝቧ ጫንቃ ላይ መቀመጡ ነው።

እስከ አሁን እንዳየነው ህወሃትን የሚመራው ሥጋና ደሙ ነው።በሥጋና ደም እየተመራ፤ ሥጋና ደም እየቆጠረ እየሾመ፤ ሥጋና ደም እየቆጠረ እየተበቀለ እስከ ዛሬ ዘለቀ። ወደፊትም ቢሆን እንደ ሰው ልጅ አስቦ ከሰው ልጆች ጋር በሠላም ለመኖር የሚችልበትን ጥበብ ይማራል ብሎ መጠበቅ አዳጋች ነው።የህወሃት ጥበቡ መዋሸት፤ መዝረፍ፤ መግደል ነው።ከህወሃት ነውሮች መካከል በጣም የሚያስገርመን ነገር ህወሃቶችና ቅጥረኞቻቸው የገዛ ውሸታቸውን አምነው ያለምንም ጭነቅት መኖር የመቻላቸው ነገር ነው። አሁን አሁንማ ሰው እውነቱን ስለሚያውቀው የህወሃቶችን ውሸት እንደ መዝናኛ እየቆጠረው ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከዓለም በኢኮኖሚ እድገት ተወዳዳሪ አልተገኘላትም፤ በምግብ ራሳችንን መመገብ ችለናል፤እኛ ያለን ሠላም ማንም የለውም፤ ዲሞክራሲያችን ለአፍሪካ በአርአያነት የሚጠቀስ ሁኗል፤ የምናካሂደው ምርጫ እንከን የለሽ ነው፤ የብሄሮች እኩልነት ከመቸውም ግዜ በላይ ተረጋግጧል ሲሉ የሰማ ሁሉ ህወሃቶችን መሳቂያ መሳለቂያ ሁነው እንዲቀሩ አድርጓቸዋል።

እስኪ ደግሞ ከሰሞኑ ዋሺንግተን ዲሲ በሚገኘው የህወሃት ኤምባሲ ግቢ ውስጥ የተፈፀመውን ድርጊት በተመለከተ ህወሃቶች ተደፈርን ያሉበትን ዋና ዋና ቁም ነገሮች እንመልከት። አንደኛው ብዙ ደም የፈሰሰለትን ባንዲራ አወረዱብን፤ ሁለተኛው ደግሞ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን አጠፉ፤ ሦስተኛው ደግሞ አባማ ስለኢትዮጵያ መሻሻል በመናገራቸው "የቀኑ" አሥራ ሁለት የሚሆኑ ጋጠ ወጦች ግቢያችንን ደፈሩብን የሚሉ ናቸው።

ህወሃቶች አሁን ደርሰው የባንዲራ ተቆርቋሪ ለመሆን በቅተዋል። ባንዲራ ጨርቅ ነው ብለው የጨውና የበሶ መቋጠሪያ እንዳላደረጉት ሁሉ ዛሬ ደግሞ ብዙ ደም የፈሰሰላትን ባንዲራ አውርደው ጣሉ እያሉ እየተንጨረጨሩ ነው። ህወሃቶች አምስት ራስ ያለው ኮከብ ያስቀመጡበትን ባንዲራ ምልክታቸው ያደረጉት ያለ ምክንያት አይደለም። ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ ያለው ኮኮብ የዳዊት ኮከብ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎቹም ከአምባሻ ጋር አያይዘውታል። እኛ ከሁለቱም ጋር ቅራኔ የለንም። በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ የተለጠፈው ባለ አምስት ራሱ ኮከብ ግን የዳዊት ኮከብ ወይም አምባሻን የሚወክል ሳይሆን በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው 666 እየተባለ ከሚታወቀው ከአውሬው መንፈስ ጋር የተያያዘ ነው።ባለአምስት ራሱን ኮከብ ማን እንዳመጣው ወይም የማን ሃሳብ እንደሆነ መቸ ለህዝብ ቀርቦ እና ህዝቡ ተወያይቶበት የኢትዮጵያ ባንዲራ እንዲሆን እንደተደረገ የሚያቅ የለም። የባለ አምስት ራሱ ኮከብ ሃሳብ ባለቤት መለስ ዜናዊ ነው። ይሄን ባለ አምስት ራሱን ኮከብ በህዝቡ ላይ የጫነው "ድርጅቱ" የሚባለው መለስ ዜናዊ ነው። መቸም ቢሆን ይሄን ባለ አምስት ራስ የኮከብ ምልክት የተደረገበትን ባንዲራ ህዝቡ እንዳልተቀበለው በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየገለጠ ይገኛል። ይሄ ባንዲራ የኢትዮጵያዊያኑ ምልክት እንዲሆን ከተደረገ ግዜ ጀምሮ ዜጎች የገቡበትን መከራ በዓይናችን የምናየው ነው። ይሄ ባለ አምስት ራሱ ኮከብ ያለበት ባንዲራ በኢትዮጵያ ምድር መከበረ ከጀመረ ጀምሮ በአገራችን በየዕለቱ የንፁህ ሰው ደም ሳይፈስ ውሎባት አያውቅም። ይሄን ምልክት የተሸከመው ባንዲራ በአገራችን መውለብለብ ከጀመረ ግዜ ጀምሮ አብሮ ለብዙ ዘመን የኖረ ህዝብ በጠላትነት እንዲተያይ ሁኗል። አብሮነት ጠፍቷል። የበቀል ስሜት እንደ ተዳፈነ እሳት በህዝቡ ውስጥ እየጨሰ ነው። ይህን ምልክት የተሸከመው ባንዲራ ለኢትዮጵያ ጥፋቷ እንጂ ደህንነቷ አይደለም። ለማንኛውም ለማነፃፀሪያነት ያክል የዳዊትን ኮከብ፤ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን የ666ን መለያ ምልክት እና የህወሃት ምልክት የሆነውን ኮከብ በሚከተለው መልኩ በምስል የቀረበውን አነፃፅሩ።



ይህ ባለ ስድስት ራሱ የንጉሥ ዳዊት ኮከብ ነው



ይህ ደግሞ የ666 ተከታዮች የሚጠቀሙበት ምልክት ነው ተብሎ የተለየው ነው። አምስት ራስ አለው። ይሄን ምልክት በተመለከተ የኃይማኖት ተመራማሪዎች ብዙ ትንታኔ ሊሰጡበት ይችላሉ።



ባለ አምስት ኮከቡ የወያኔ ባንዲራ

ወያኔ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ባንዲራችን ላይ የለጠፈዉ ይህንኑ አምስት ራስ ያለዉን ኮከብ ነው። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ህወሃትና አባላቱ የሚሠሩት ለዚህ ምልክት ባለቤት ለሆነው አካል ነው። ይሄን ምልክት የጠሉ፤ ይህ ምልክት በኢትዮጵያ ላይ ከቆመ ግዜ ጀምሮ በአገራችን ላይ የደረሰው ግፍ ያስቆጣቸው ሰዎች ባንዲራውን በማውረድ ቁጣቸውን ገልፀዋል። እንግዲህ ማንኛውም እግዚአብሄርን አመልካለሁ የሚል ሁሉ የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ የተለጠፈው የሰይጣን ምልክት እንዲነሳ ብቻ ሳይሆንም የምስሉ ባለቤት ነን የሚሉት ህወሃቶችም ከህዝቡ ጫንቃ ላይ እንዲወርዱ መታገል ግዴታው ይሆናል ማለት ነው።

ሌላው ህወሃቶች ሊነግሩን የሚፈልጉት "ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን" በተመለከተ ነው። ለመሆኑ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት እንዴት ይገለፃል? በአጭሩ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የሚገለፀው ሰው ምን ይለናል፤ እግዚአብሄርስ ምን ይለናል በሚሉ ማህበረሰቡን በሥነ-ምግባር አፅንተው ባቆዩ ሁለት ምሰሶዎች ነው። ህወሃት ኢትዮጵያን ከመቆጣጠሩም ሆነ ከተቆጣጠረ ግዜ ጀምሮ የሚታወቀው እነዚህን የማህበረሰባችንን ምሰሶዎች በመናድ ነው።የህወሃቶች ጥረት በተወሰነ ድረጃ ተሳክቶላቸው ግርማ ብሩን የመሰለ የወገኑን ጨኸት ለመስማት ፍላጎት የሌለውን ሆድ አደር አደር ባይን ለመፍጠር ችለዋል።

ዛሬ ብዙ አደርባዮች፤ ብዙ ስግብግብ፤ ብዙ እኔ ብቻ እንጂ ወገን አገር የሚለውን የማያውቁ ዜጎች ተፈጥረዋል። ራሱ ድርጅቱ አደርባይነት የህልውናችን አደጋ ነው ብሎ እንዲናገር እስከሚገደድ ድረስ ደርሷል። ግርማ ብሩ ከደርግ ጋር ሁኖ ህወሃቶች ሲያማ የቆየ፤ ኋላም ህወሃቶች በለስ ቀንቷቸው ሰይጣናዊ አርማቸውን ተሸክመው አዲስ አበባ ሲገቡ ተከትሏቸው ሲጠሩት አቤት፤ ሲልኩት ወደየት እያለ የሚኖር የአደርባዮች መልካም ምሳሌ የሆነ ግለሰብ ነው። ይህ ግለሰብ ከድሆች ጉሮሮ ላይ እየሰረቀ ባከማቸው ገንዘብ ከሚሊየነሮች ጎራ የተቀላቀለ፤ በዚህም ስብዕናውን ለህወሃቶች አሳልፎ ሰጥቶ የገዛ ውሸቱን አምኖ ከሚኖሩ በሽተኞች መካከል አንዱ ነው። ይሄን በመሰለ የሞራል ውድቀት የሚኖር ከንቱ ግለሰብ እናናግርህ ያሉትን ወጣቶች "ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደላቸው"ብሎ ሲሳደብ አለማፈሩ ራሱ ያሳፍራል። ግርማ ብሩ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ቢኖረው ኑሮ እናናግርህ ያሉትን ወገኖቸ የሚሉትን ለማድመጥ በሩን በከፈተ ነበር። እንዲያ ቢያደርግ ኑሮ ተኩስም ባልተከፈተ አገራችንም እንዲህ መሳለቂያ ባልሆነች ነበር። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

# ወያኔ ሲያስር አሜን....ሲገድልም አሜን ( በኤፍሬም ማዴቦ )

ብዕር የያዘ ማንም ሰዉ በዘመናችን ደግሞ የኮምፒተር መክተቢያ ፊቱ ላይ የደቀነ ሁሉ ከሱ ዉጭ ያለዉን ማንንም ሰዉ "ሌባ"፤ "ባንዳ" ወይም "ከሃዲ" እያለ እንዳሰኘዉ መጻፍ ይችላል። በተለይ በእንደኛ አይነቱ ሀላፊነትም ተጠያቂነትም በሌለበት ህብረተሰብ ዉስጥ ደግሞ የጓደኛዉ ሀሳብ ያልተስማማዉ ሁሉ እየተነሳ የገዛ ጓደኛዉን ባንዳና ከሃዲ አድርጎ ስለሚስለዉ የላይ የላዩን ብቻ ለሚመለከት ሰዉ አገራችን በባንዳና በአገር ወዳድ መሳ ለመሳ ለሁለት የተከፈለች ትመስላለች። እግዝአብሄር ይመስገን እዉነቱ ግን ከዚህ እጅግ በጣም የተለየ ነዉ። ርዕሴን የጀመርኩት አሜን ብዬ ነዉና እስኪ አንባቢዉ አንተም አሜን በል። ባንዳነትና ከሃዲነት ኃብታምና በእድገት ወደፊት የገፉ አገሮችን እየዘለለ ደሃና ኋላ ቀር አገሮችን ብቻ የሚጠናወት ተራ በሽታ አይደለም። ብዙዎቻችን አምባገነን መሪዎቻችንን ሸሽተን የተጠለልንባት አገር አሜሪካ እነ ሄንሪ ቤስትንና ጆን ብራዉንን የመሳሰሉ ከሃዲዎችን እንዳበቀለች ሁሉ ኢትዮጵያችንም ትናንት እነ ኃ/ሥላሤ ጉግሳን ዛሬ ደግሞ የኃ/ሥላሤ ጉግሳ የልጅ ልጆች የሆኑትን እነ መለስ ዜናዊን፤ አባይ ፀሐዬንና ሰብሃት ነጋን የመሳሰሉ የለየላቸዉ ከሀዲዎችን አፍርታለች። በነገራችን ላይ ሙስሊሙ በዱአዉ፤ ክርስቲያኑ በፀሎት፤ ጠቢብ በጥበቡ ፤ፀሐፊ በምናቡ የባንዳዉንና የከሃዲዉን ብዛት ለመቀነስ ካልተባበሩ በቀር "ወላድ በድባብ ትሂድ" ብለን ባንመርቃቸዉም የባንዳ አባትና እናት አስካሉ ድረስ ባንዳም መወለዱ አይቀርም።

ደጅአዝማች ኃ/ሥላሤ ጉግሳ ማንም ሳያስገድደዉ ወድዶና ፈቅዶ ለወራሪዉ የጣሊያን ጦር ካደረ በኋላ ከጄኔራል ደቦኖ ጋር ሆኖ እናት አገሩን ኢትዮጵያን ወግቷል። ጣሊያኖች ኃ/ሥላሤ ጉግሳ ከነተከታዮቹ ከጎናቸዉ ተሰልፎ አገሩን ሲወጋ ያደረጉት የመጀመሪያዉ ነገር ይህ ከሃዲ ሰዉ ከጎናቸዉ መሰለፉን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ለዓለም ህዝብ ማሰራጨት ነበር። ታሪክ እራሱን ይደግማል ሲባል አይኑ አላይ እያለዉ በጆሮዉ ብቻ ለሰማ ሰዉ ዛሬ ማረጋገጫዉ እነሆ በግልጽ ቀርቦለታል። ትናንት ማክሰኞ መስከረም 27 ቀን የወያኔ ቴሌቭዥንና ሬድዮ ኢትዮጵያ ዉስጥ በጋዜጠኞች ላይ የሚፈፀመዉን እስርና ስደት፤ ወያኔ በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽመዉን የዕለት ከዕለት ሰቆቃና እንዲሁም በቅርቡ አምቦና አጋዴን ዉስጥ የተካሄዱትን የጅምላ ግድያዎች የሚደግፉ የዚህ ዘመን ኃ/ሥላሤ ጉግሳዎች ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ያካሄዱትን የክህደት ሰለማዊ ሠልፍ በተደጋጋሚ ለህዝብ አቅርበዋል። እነዚህ ትናንት ክቡር ባንዲራችን በአለባሌ ሰዉ አንደበት "ጨርቅ" ተብላ ስትሰደብ ከተሳዳቢዉ ሰዉ ጎን ቆመዉ የሳቁና የተሳለቁ ከሃዲ ሆድ አምላኪዎች ዛሬ "ባንዲራችን ተደፈረ" ብለዉ የአዞ እምባ ያነቡብናል። የትኛዉ ባንዲራ? ለመሆኑ እነዚህ "እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነዉ" ባዮች ጀግናዉ ዘርዐይ ደረስ ጣሊያኖችን በራሳቸዉ አደባባዮች አንገታቸዉን በጎራዴ የቀላዉ ለዬትኛዉ ባንዲራ እንደሆነ ያዉቃሉ? እነ አብዲሳ አጋ፤ በላይ ዘለቀ፤ ባልቻ አባ ነብሶና እልፍ አዕላፋት የኢትዮጵያ ልጆች ምትክ የሌላትን ህይወታቸዉን የሰጡት ለዬትኛዉ ባንዲራ አንደሆነ ያዉቃሉ?

እነዚህ ወያኔ አዲስ አበባ ዉስጥ የገዛ ወገኖቻቸዉን ሲያስርና ሲገድል አሜን ብለዉ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ሠላማዊ ሠልፍ የሚወጡ የለየላቸዉ ከሃዲዎች ባንዲራ አዲስ መንግስት በመጣ ቁጥር እንደ ፖሊሲና እንደ ካቢኔ ሚኒስቴር የማይቀያየር ቋሚ የአገር ማንነትና የትዉልድ ትስስር መታወቂያ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ባንዲራ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ሊቀየር ይችላል ብለን ብናስብ እንኳን ምን አይነት ሰዎች ብንሆን ነዉ ባንዲራን የመሰለ ህዝብና አገር ማስተሳሰሪያ ማተብ ኢትዮጵያንና ታሪኳን ከልቡ ለሚጠላዉ መለስ ዜናዊና የትግራይ ሪፓብሊክ ካላቋቋምኩ ብሎ ይታገል ለነበረዉ ለከሃዲዉ ስብሀት ነጋ የምንተዉላቸዉ? ደግሞም እነዚህ ምናምንቴዎች አንደሚሉት ባንዲራችን ላይ ባዕድ አካል ሆኖ የተለጠፈዉና የኢትዮጵያ ህዝብ በተለምዶ "ባላ አምባሻዉ" እያለ የሚጠራዉ የወያኔ ጨርቅ እዉነትም ኢትዮጵያ ዉስጥ የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት አረጋግጦ ቢሆን ኖሮ ዛሬ አገራችን በየቀኑ ብሄር ብሄረሰቦች ዉጣልኝ አልወጣም እየተባባሉ የሚተላለቁባት አገር አትሆንም ነበር። አባቶቻችን የሞቱት ለአረንጓዴ፤ ብጫና ቀይ ባንዲራ ነዉ፤ እኛም ዛሬ በየተሰደድንበት አገር አገሬን እያሰኘ የሚያስጮኸን ይሄዉ አረንጓዴ፤ ብጫ ቀይ ባንዲራችን ነዉ። አገር ቤት ያለዉ ኢትዮጵያዊም አንዱን "ባላአምባሻዉ" ሌላዉን ደግሞ ባንድራዬ እያለ የሚጠራዉ ይህንኑ አረንጓዴ፤ ብጫና ቀይ ባንዲራዉን ነዉ። በአንዲት አገራችን ኢትዮጵያ ዉስጥ እነሱም እኛም ለየቅላችን የኛ የምንለዉ ባንዲራ ሊኖር በፍጹም አይችልም። ይልቅ ወያኔዎች ሲጠፉ እነሱ ይዘዉብን የመጡት ኮተቶ ሁሉ አብሯቸዉ መጥፋቱ አይቀርምና ዛሬ "ባንዲራችን ተደፈረ" ብላችሁ የምታቅራሩ እዉሮች ነገ ከወያኔ በጸዳችዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ጭራሽ ባንዲራ ላይኖራችሁ ይችላልና መጀመሪያ ከራሳችሁ ጋር ቀጥሎም ከአገራችሁ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትታረቁ አጥብቄ እማጸናችኋለሁ።

የወያኔን ቂልነትና ባዶነት ባሰብኩ ቁጥር ትዝ የምትለኝ አንዲት ቀልድ ብጤ አለችኝ ፤ እስኪ ለፈገግታ ትሆናለችና አዳምጡኝ። ሁለት አመት የፈጀዉ የኤርትራና የኢትዮጵያ አላስፈላጊ ጦርነት እንዳለቀ በጦርነቱ ወቅት ስንቅና ትጥቅ በማመላለስ ትልቅ ዉለታ የዋለች ኣንዲት አህያ ጦርነቱ አብቅቶ የድል በዐል ሲከበር መስቀል አደባባይ ተጋብዛ መለስ ዜናዊ ፊት ትቀርባለች፤ በቋንቋ ይግባቡ ነበርና መለስ ጎንበስ ብሎ በጆሮዋ አንድ ነገር ሹክ ሲላት አህይት በደስታ እየፈነጠዘች አደባባዩን መዞር ጀመረች። በልማታዊ አህይት ዝላይና ፍንጠዛ ግራ የተጋቡት የወያኔ ጋዜጠኞች ዜና ያገኙ መስሏቸዉ "ታላቁ መሪ" ምን አለሽ ብለዉ አህይትን ጠየቋት። የዕድሜ ልክ የህወሓት አባል ሆነሻል ተብያለሁ ብላ አህይት ዝላይዋንና ፍንጠዛዋን ቀጠለች።

ትናንት እዚህ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ የወያኔን ጭፍጨፋ፤ እስርና በዘር መድሎ የተጨማለቀ ስርዐት አበጀህ ቀጥልበት ብለዉ አደባባይ የወጡ ጥቂት ህሊና ቢሶችና እነሱን አመስግኖ የነጻነት አርበኞችን "ዱሪዬዎች" ብሎ የዘለፈዉ የአድር ባዮች ሁሉ አድርባይ የሆነዉ ግርማ ብሩ ከዚያች ባድመ ላይ ብዙ ስንቅና ትጥቅ ካመላለሰችዉ ጎበዝ አህያ የሚለዩበት መንገድ ቢኖር አህያዋ ማሰብ ስለማትችል አለማሰቧ እነሱ ግን ማሰብ እየቻሉ አለማሰባቸዉ ብቻ ነዉ። በተረፈ እነሱም አህያዋም የወያኔ አባልነታቸዉ ያስደስታቸዋል፤ ምክንያቱም ሁለቱም አያስቡም። መቼም የገዛ ወንድሙና እህቱ ሲታሰሩ፤ ሲደበደቡና ሲገደሉ አሜን ብሎ ተቀብሎ ነብሰ ገዳዮችን ደግፎ ሰላማዊ ሠልፍ የሚሰለፍ የሰዉ ዘር ያለዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ መሆን አለበት። ለዚያዉም በወያኔ ዘመን ብቻ!

እነዚህን ሆዳሞች ደግሜ ደጋግሜ እዉሮች እያልኩ የምጠራቸዉ አለምክንያት አይደለም። በእርግጥም ስለማያዩ ነዉ። ባለፈዉ ወር እዚህ አሜሪካ ሚዙሪ ግዛት ፈርግሰን የሚባል ከተማ ዉስጥ ከባድ መሳሪያ የታጠቁ ፖሊሶች መሳሪያቸዉን ሰላማዊ ሰልፈኛዉ ላይ ስላዞሩ (ልብ በሉ ስላዞሩ ነዉ ያልኩት እንጂ ስለተኮሱ አላለኩም እነሱም አላደረጉትም) የአሜሪካ ህዝብ፤ መሪዎችና የህዝብ ተወካዮች ምን ያህል እንደተንጫጩ ሁላችንም ተመልክተናል። እነዚያ እዉሮች ያልኳቸዉ ወንድሞቻችንም እኛ የተመለከትነዉን ተመልክተዉት ይሆናል፤ ግን እነሱ የአዕምሮ እዉራን ናቸዉና ስዕሉን ብቻ ነዉ እንጂ ቁም ነገሩን አላዩትም። ስለዚህም ነዉ የነሱ ድፕሎማት ተብዬዉ ድንጋይ ራስ (ርዕስ እምኒ) አዲስ አበባ ዉስጥ ያለ መስሎት ሠላማዊ ሠልፈኛ ለመግደል ደጋግሞ ሲተኩስ አበጀህ ብለዉ ሠላማዊ ሠልፍ የወጡለት። እግዚአብሄር ከዚህ አይነቱ የአዕምሮ እዉርነት ያድነን! እባካችሁ አሁንም አሜን በሉ። እኔ እያረረ የሚስቅ ማሽላ ብቻ ይመስለኝ ነበር . . . . ለካስ የገዛ ወገኖቹ ሲገደሉ ደስ ብሎት የሚስቅ ሰዉም አለ። አቤት እግዚኦ!!!!

ሌላዉ የገረመኝ ነገር ቢኖር እነዚህ የአዕምሮ እዉራን ትናንት ረፋዱ ላይ ለአሜሪካዉ ዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጆን ኬሪ በጻፉት ደብዳቤ ግንቦት 7 ያ እንቅልፋም ፓርላማቸዉ "ሽብርተኛ" ብሎ የፈረጀዉ ድርጅት ነዉና ምነዉ ዝም ብላችሁ ታያላችሁ ብለዉ ኬሪን መወትወታቸዉ ነዉ። ኬሪ እንደነሱ ጨካኝና አምባገነን መሪዎች የማይወደዉንና የሚጠላዉን ሁሉ አይንህ አላማረኝም እያለ ማሰር የሚችል መሰሏቸዋል። እነዚህ ሆዳቸዉ ልባቸዉን የሸፈነ ከሃዲዎች አይገባቸዉም አንጂ የነሱን "ግንቦት ሰባቶችን" እሰሩልን ብሎ ጥያቄ እንኳን ኬሪ የአለማችን ሀይለኛዉ መሪ አባማም ማስተናገድ አይችልም። እኛስ ብንሆን የምንታገላቸዉ ለዚሁ ነዉኮ - ኢትዮጵያን የሚመራ ሁሉ ሀሳባችን ከሀሳቡ በተጋጨ ቁጥር አንዳያስረንና እንዳይደገድለን። እኔኮ ምን ይሻለኛል . . . . በአንድ በኩል ኢትዮጵያዉያን የወገኖቻቸዉን መገደል ተቃዉመዉ ሠላማዊ ሠልፍ ሲወጡ የወያኔዉ ተላላኪ ግርማ ብሩ የኤርትራን መንግስት ይከስሳል፤ የአይጥ ምስክር ድንቢጥ እንዲሉ የግርማ ብሩ ተላላኪዎች ደግሞ (የተላላኪ ተላላኪ ማለት ነዉ) ግንቦት ሰባት የሚረዳዉ በኤርትራ መንግስት ነዉና ስጋታችንን እዩልን እያሉ ኬሪን ይለማመጡታል። መቼም አዉቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይነቃም ነዉና የወያኔ ደጋፊዎች አይገባቸዉም አንጂ ለሻዕቢያ ጎንበስ ቀና እያሉና የሻዕቢያን መሪዎች እንደ አክሱም ፅዮን እየተሳለሙ ለዚህ ዛሬ ላሉበት ደረጃ የበቁት የወያኔ መሪዎች ናቸዉኮ። ዛሬ በባነኑ ቁጥር አንዴ ግንቦት ሰባት አንዴ ሻዕቢያ እያሉ ዛር እንደያዘዉ ሰዉ የሚያጓሩትም ተደምስሰዉ ከታሪክ ምዕራፍ የሚፋቁት በዚሁ እንደ ህጻን ልጅ እጃቸዉን ይዞ ለታሪክ ባበቃቸዉ በሻዕቢያ በኩል መሆኑን በሚገባ ስለሚያዉቁት ብቻ ነዉ። ምድረ የወያኔ አጎብጋቢዎች ዛሬ እቅጩን ልንገራችሁ፤ ወደዳችሁም ጠላችሁ ይህ "ልማታዊ" ብላችሁ የምትጠሩት ነብሰ ገዳይ አገዛዝ ይደመሰሳል- ስጋታችሁ ትክክለኛ ስጋት ነዉ። ግን ከዚህ ስጋት የሚያድናችሁ ኬሪ ሳይሆን የራሳችሁ ሂሊና ብቻ ነዉና ሳይዉል ሳያድር ዛሬዉኑ ኑና ከህዝብ ጎን ተሰለፉ፤ አለዚያ ዕድላችሁ ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ይሆናል። መቼም እንደኔዉ የዚያች ምስኪን አገር ልጆች ናችሁና በተረት ብነግራችሁ ይገባችኋል ብዬ ነዉ እንጂ በእናንተና መወቀጥ በሚገባዉ ኑግ መካከል ምንም ልዩነት የለም።

የዘረኞቹ የወያኔ መሪዎችና እንደ ችግኝ ኮትኩተዉ ያሳደጓቸዉ ቡችሎቻቸዉ አስቂኝ ታሪክ በዚህ ብቻ አያበቃም፤ እነዚህ ጣምራ ጉደኞች ብዙ ተነግሮ የማያልቅ ጉድ አላቸዉ። ወያኔዎች ጋዜጠኛ እያሰሩና ከአገር እንዲሰደድ እያደረጉ ተዉ ያላቸዉን ፀረ አገርና ፀረ ልማት ይሉታል፤ በየሰላማዊ ሠልፉ ላይ ንጹህ ዜጎችን በጅምላ ሲጨፈጭፉ ምነዉ ያላቸዉን ደግሞ ሽብርተኛ ብለዉ ያስሩታል። እነዚህ አረመኔዎች ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ጋጠ ወጡ ማን ነው ?

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንግዲህ ጋጠ ወጡ የሠላማዊ ተቃቃሚዎች ላይ ተኩስ የከፈተውን ነፍሰ ገዳይ የፈጠረ ሥርዓት እንጂ ወገኖቼ ተጎዱ ብሎ የሚጮህ ዜጋ አይደለም።

ሌላው የተቃውሞው ምክንያት አድርገው ለማቅረብ የሞከሩት የኦባማን ንግግር ነው።ኦባማ ዲፕሎማሲያዊ ጨዋነት ከሚጠይቀው በታች ወርደው በኢትዮጵያ ሁሉም ተንበሽብሿል ማለታቸው ብዙ ኢትዮጵያዊያንን ማስቆጣቱ የሚካድ አይደለም። ጠሙን ውሎ፤ ጠሙን ለያሚያድረው ህዝብ ኢኮኖሚው በፈጣን ሁኔታ እያደገ ነው ማለታቸው በሰው ቁስል እንጨት እንደመስደድ ይቆጠራል። የኦባማ ንግግር እውነተኛውን የኢትዮጵያን ገፅታ የማይገልፅ በመሆኑ ብዙ ኢትዮጵያዊን አዝነዋል። በዲሲ የህወሃት ኤምባሲ ውስጥ የተገለፀው ቁጣ ግን መነሻው ይሄ አይደለም። መነሻው ጠባብ ዘረኝነት የወለደው አድልዎ፤ በኦጋዴን እና በጋምቤላ እየተፈፀመ ያለው የዘር ማጥፋት፤ በአገሪቷ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ዝሪፊያ፤ የዜጎች ስደት እና እንግልት፤ፈፅሞ ከእውነት የተጣላ ቡድን አገሪቷን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠሩ አገሪቷ የገባችበት ቀውስ ነው።አደር ባዩ ግርማ ብሩ ግን አገሪቷ ውስጥ ያለው አስከፊ ሁኔታ ያስቆጣቸውን ኢትዮጵያዊያኑን "ኦባማ ስለ ኢትዮጵያ በጎ ነገር በመናገራቸው የቀኑ "ሲል ገልፆታል። ግርማ ብሩ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ኦባማ እንደሚሉት ከዓለም ሁሉ በፈጣን ሁኔታ እያደገ አለመሆኑን ደህና አድርጎ ያውቃል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አድጎ አገሪቱ ከልመናና ከብድር ብትወጣ የሚቀና ኢትዮጵያዊ እንደማይኖር ግርማ ብሩ አያውቅም ማለት አይቻልም። ግርማ ብሩ ከእውነት ይልቅ ለሆዱ ያደረ በመሆኑ በቁስላቸው እንጨት የተሰደደባቸውን ኢትዮጵያዊያንን "በኢትዮጵያ እድገት የቀኑ" የሚል ስድብ ለጥፎባቸዋል። ከህወሃት መንደር ከዚህ ውጪ አይጠበቅም። ህወሃትና የሰበሰባቸው አደር ባዮች የገዛ ውሸታቸውን አምነው የሚኖሩ ጋጠ ወጦች ሆነው ሳለ ሌሎቹን ጋጠ ወጥ ብለው መሳደባቸው ግለሰቦቹ በህልም ዓለም እንደሚኖሩ አንዱ ማሳያ ነው።

እንግዲህ ምን ቀረን? ተባብሮ ይህን የሰይጣን ምልክት መለያቸው አድርገው፤ አገሪቷን ከሚያጠፍ ህዝቡንም ከሚያዋርዱ ጠባብ ዘረኞች እጅ አገራችንን ማለቀቅ ግዜው የሚጠይቀው ሃይማኖታዊም ሆነ የዜግነት ግዴታችን ነው። ዜጎች ስለኃይማኖታችሁ ስትሉ፤ ስለ ክብራችሁ ስትሉ፤ስለ አገራችሁ ኢትዮጵያ ስትሉ ህወሃት ከተቆናጠጠበት ወንበር እንዲወርድ የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ተነሱ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## ወያኔ የመከላከያ ሰራዊቱ ህብረብሄር ሆኗል ሲል

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግንቦት7 በጥናቱ ከ10 ከከፍተኛ ወታደራዊ እዝና ቁጥጥር ዘርፎች የበላይ ሃለፊዎች ከሆኑት 10 ባለስልጣኖች ውስጥ 9ኙ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ናቸው።ጄል ሳሞራ፣ ሌ/ጄ ሰአረ መኮንን፣ ሜ/ጄኔራል ኢብራሂም አብዱጀሊል፣ ብ/ጄ ገብሬ ዲላ፣ ሜ/ጄ ብርሃኔ ነጋሽ፣ ብ/ጄ ክንፈ ዳኘው፣ ሌ/ጄ ዮሃንስ ገ/መስቀልና ብ/ጄ መሃመድ ኢሻ የትግራይ ብሄር ተወላጆች ሲሆኑ፣ ሜ/ጄ አደም መሀመድ ብቻ የአማራ ተወላጅ መሆናቸውተጠቅሷል። ከኦሮሞና ከሌሎች ብሄሮች አንድም በከፍተኛ ወታደራዊ አዛዥነት የተቀመጠ ሰው የለም። ከአምስቱ የእዝ ሃላፊዎችም 4ቱ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ፣ አንዱ ከኦሮሞ መሆኑ በጥናቱ ተጠቅሷል። ከምድር ጦር ክፍል ከማእከላዊ እዝ ከ6ቱ አዛዦች 4ቱ የትግራይ ተወላጆች ሲሆኑ፣ አንዱ የአማራ ሌላው የአገው ተወላጅ መሆናቸው ተመልክቷል። ከሰሜን እዝም እንዲሁ ከ6ቱ ሁለቱ ብቻ የሌላ ብሄር ሲሆኑ ሌሎቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ከደቡብ መስራቅ እዝ ሁለት ኦሮሞ፣ ሁለት ትግሬና አንድ አማራ የሚገኙ ሲሆን፣ ከምእራብ እዝ ሁለትትግሬ፣ አንድ ኦሮሞና አንድ ድብልቅ እንደሚገኙ በጥናቱ ተጠቅሷል።

በመከላከያ ሚኒስቴር የውጊያ አገልግሎትና ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ውስጥ 13 ትግሬዎች፣ አንድ አማራና አንድ ኦሮሞ እንደሚገኙ ጥናቱ አሳይቷል። ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያ አዛዦች ውስጥ ከ10 ባለስልጣነቱ ውስጥ 7ቱየትግራይ ተወላጆች ናቸው። በሌላ ዜና ደግሞ ገዢው ፓርቲ እያንዳንዱ የቀበሌ ሊ/መንበር እስከ 15 ወታደሮችን መልምሎ እንዲያመጣ መተዛዘዙን የደረሰን መረጃ ያመለክታል። መከላከያን ጥለው የሚጠፉ ወታደሮችመጨመራቸው ለሰራዊት ምልመላ መነሻ መሆኑን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ማንኛውም ከ8ኛ ክፍል በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው ሰው እንዲመለመል መመሪያው ያዛል።

## በረከት ስምኦን በእዉቀት የሚበልጡትን የዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በእለቱ የዩኒቨርስቲ መምህራኑ ካነሱዋቸው ጥያቄዎች መካከል " እንደ ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሁሉ በየቀበሌዉ ሰባዊ መብቶች እየተጣሰ ስለሆነ የሰብዓዊ ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ለምን መብት እንዲያስተምሩ አይመደቡም? የሁሉም ችግሮች እናት መንግስት የግል ተቋም (privatization of state) መሆኑ እየታወቀ ኢህአዴግ ለምን እራሱን አይፈትሽም? ኢህአዴግ የዩኒቨርሲቲ ተማሪችን ስራ ለማስቀጠር አባል ማድረጉ ምን ድረስ ያስኬደዋል? ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ መሬት ለሱዳን ለምን ተሸጠ?

አማራዎችና አማርኛ ተናጋሪ ኦሮሞዎች ለምን በወረዳና ቀበሌ አስተዳዳሪዎች ከተለያዩ ቦታዎች እንዲፈናቀሉ ይደረጋል? የአንድ ለአምስት አደረጃጀት እንዴት ግሩፕ መመስረት እንዳለብን ለምናዉቅ የዩኒቨርሲቲ፣ መምህራን በአስገዳጅ መልኩ መጫን ምን ማለት ነዉ?ኢህአዴግ ከ97 ዓ.ም በኋላ ልማት እንጅ ዴሞክራሲን ወደ ጎን ለምን ተወ? ህዝቡን እንደዚህ አናክሳችሁ ኢህአዴግ በድንገት ስልጣን ቢለቅ የሀገሪቱ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ነዉ ? የሚሉት ይገኙበታል። ኢህአዴግ ልማታዊ ብሄርተኝነት እንጅ ልማታዊ መንግስት አይደለም" የሚል አስተያየትም ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ዜና በአዲስ አበባ በሚካሄደው የኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጠና መድረክ ላይ ከተሳታፊዎች ለመድረክ አወያዮች የሚቀርቡት ጥያቄዎች ተጠናክረው እንደቀጠሉ ነው።

ኢህአዴግ በአዲስ አበባ የድርጅት አባላቱን ከአዲስ አመት በፊትና በኋላ ለ13 ቀናት በመጀመሪያ ዙር ካሰለጠነ በኋላ፣ ለሁለተኛ ዙር ደግሞ ለ11 ቀናት በሚቆይ ጊዜ ጥቂት ያልሰለጠኑ አባላትን እና መላ አባል ያልሆኑትን የመንግስት ሠራተኞች ማሰልጠን ከጀመረ አንድ ሳምንት ተቆጥሯል። ለአዲስ አበባ መስተዳደር ተጠሪ መ/ቤት ሠራተኞች በእንጦጦ ቴክኒክና ሙያ መለስተኛ አዳራሽ፣በሃገር ፍቅር ቲያትር ቤት አዳራሽ እና ለፌደራል ተጠሪ መ/ቤት የመንግስት ሠራተኞች ደግሞ በአዲስ አበባ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ግቢ ውስጥ እዚያው እያደሩና እየሰለጠኑ የሚገኝ ሲሆን ከስልጠናው ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ለተሳታፊዎች የሚያስፈልጋቸውን አበል በስልጠናው አጋማሽ ላይ ለላኳቸው መ/ቤቶች ከኢህአዴግ ጽ/ቤት ቀጥታ ስልክ በመደወል ከመንግስት ካዝና በአስቸኳይ አበል እንዲዘጋጅላቸውና ክፍያ እንዲከፈል የተደረገ ሲሆን፤ በመቀጠል በሁሉም የስልጠና ቦታዎች ከስልጠናው ተሳታፊ የመንግስት ሠራተኞች የሚቀርበው ጥያቄ ለኢህአዴግ አወያይ ካድሬዎች ከአቅም በላይ እንደሆነባቸውም ለማዎቅ ተችሏል። አንዳንድ የስልጠናው ተሳታፊዎች እንደሚሉት ኢህአዴግ ከስልጠናው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተመጣጣኝ ምላሽ ሳይሰጥ እዚያው በስብሰባው ላይ በተዘጋጀው የ1 ለ 5 ቡድን ላይ በጋራ ተወያዩበት እያለ እንደሚገኝ እና በዚሁ የ1 ለ 5 ቡድን ላይም እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ በማድረግ በስብሰባው ላይ ንቁ ተሳታፊ ለሆነ ጥሩ ነጥብ፣ ንቁ ተሳታፊ ላልሆነ ደግሞ ዝቅተኛ ነጥብ እንዲሰጥ እያደረገ ነው። ኢህአዴግ በስልጠና በመድረኮቹ ላይ ትኩረት ያደረገው ከተሳታፊዎቹ በተናጠል ለሚነሱ ጥያቄዎች እንጂ ለሚመለሰው መልስ እንዳልሆነ ለማዎቅ ተችሎአል። በተሳታፊዎች ከተነሱት ጥያቄዎች መካከል "ኢህአዴግ ራሱን ብቻ ታሪክ ሰሪ አድርጎ የሌሎቹን መንግስታት ታሪክ እንዲጠፋ ይፈልጋል፤ ህዝቡን እንደማያቅ በመቁጠር ነፃ ጋዜጦችን በሰበብ አስባብ ከገበያ በማስወጣት ህዝቡ የደርጅቱን ታማኝ ፕሬሶች ብቻ እንዲከታተል እያደረጋችሁ ነው፤ እንዴት አንድ እንኳ ነፃ ጋዜጣ እንዲኖር አታደርጉም፤የሃይማኖት እኩልነት አለ እያለችሁ፣ መንግስት በሃይማኖት ውስጥ እጁን አላስገባም እያላችሁ በተግባር ግን ሲታይ ከእጃችሁ አልፎ መላ

አካላታችሁ በተለይ በእስልማነ ሃይማኖት ውስጥ በግልጽ አስገብታችኋል፤ መስኪዶችን በጠራራ ጸሃይ ታሽጋላችሁ፤ የፌደራል ልዩ ሃይል ፖሊሶች የሚመሩበት ህግ አለ ወይ? የትምህርት ፖሊሲውን አጥፍታችሁታል፤ ለይስሙላ ምርጫ ብላችሁ ብዙ ሃብትከምታባክኑ ወደ ለየለት ጭቆና ብትገቡ አይሻልም ወይ፤ እናንተ በመጣችሁበት መንገድ በታጣቂ ሃይል ካልሆነ በስተቀር በምርጫ የምትለቁ አይመስልም፤ እናንተ የምትመሩበት የፖለቲካ ርእዮት አለም ግልጽ ሳይሆን የምዕራባዊያንን የፖለቲካ ሪዕዮትአለም በጅምላ ታጥላላችሁ" የሚሉት ይገኙበታል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አዲሱን ዓመት አስመልክቶ . . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

## ወያኔ ሲያስር አሜን....ሲገድልም አሜን

. . . ( ከገጽ 2 የዞረ )

ይህንን የመሰለ ለጆሮ የሚቀፍ ወንጀል በህዝብና በአገር ላይ ፈጽመዉ ሰዎች በነጻነት ወደሚኖሩበት አገር ሰዉ መስለዉ ሲመጡና ስንቃወማቸዉ ደግሞ እዚህ ዉጭ አገር ያስቀመጧቸዉ ተናካሽ ዉሾቻቸዉ "ኢትዮጵያዊ ጨዋነት" የጎደላቸዉ ብለዉ ይዘልፉናል። ለመሆኑ ለእነዚህ እንደ ዉሻ ቁራሽ ስጋ በተወረወረላቸዉ ቁጥር ለሚያላዝኑ ምናምንቴዎች ማነዉ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት እንደነሱ ነዉርን አሜን ብሎ መቀበል ብሎ የነገራቸዉ? ዜጎችን አንደ እንስሳ አየጎተቱ ገድለዉ አስከሬኑን በሚቹ ወንድም እያስጎቱና ይህንን ነዉር በቪድዮ እየቀረጹ መሳቅና መሳለቅ ነዉ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ወይስ  ይህንን ኔሮና ሂትለር ምን አደረጉ የሚያሰኝ ጭካኔና አረመኔነት መቃወም ነዉ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት? አዲስ አበባ ዉስጥና እዚህ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ተቃዋሚ ኃይሎችን "ኢትዮጵያዊ ጨዋነት" የጎደላቸዉ ብለዉ የዘለፉት ሬድዋን ሁሴንና ግርማ ብሩ የዉኃ ጠብታን ያክል ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በደማቸዉ ዉስጥ ቢኖር ኖሮ "ኢትዮጵያዊ ጨዋነት" የኢትዮጵያዉያንን ህይወት በየአደባባዩ መቀማት አይደለምና እናከብራቸዉ ነበር እንጂ በወጡና በገቡ ቁጥር ስማቸዉን እየጠራን ሌባና ከሃዲ እያልን አናሸማቅቃቸዉም ነበር። ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ስንታሰርና ስንዋረድ እልል፤ ስንገደል ደግሞ አሜን ብለን እንደ በሬ አንገታችንን ለቢለዋ መስጠት ማለት አይደለም። ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለወገን ማዘን ነዉ፤ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ወገን ሲጎዳና ሲጠቃ ከለላ መሆን ነዉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ዜጎች ሰቆቃ ሲፈጸምባቸዉና ሲገደሉ ቆሞ ከመመልከት ይልቅ ወይም የገዳዮች ጠበቃ ከመሆን ባጭር ታጥቆ  ነብሰ ገዳዮችንና የጭካኔ ምልክቶችን ከአገር አናትና ከህዝብ ጀርባ ላይ ማስወገድ ነዉ - ወላድ በድባብ ትሂድ - ይህንን የሚያደርጉ የቁርጥ ቀን ልጆች እናት ኢትዮጵያ ትናንንት ነበሯት፤ ዛሬ አሏት ነገም ይኖሯታል።

ebini23@yahoo.com

## ወያኔ "ጨርቅ" ብሎ የሰደበዉን ባንዲራ ለማክበር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሚሰራበት በአል ነው በማለት አስተያየታቸውን የተጠየቁ ወገኖች መመለሳቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።«ባንዲራ ጨርቅ ነው» በማለቱ ከፍተኛ የህዝብ ተቃውሞና ቁጣ ተቀስቅሶበት የቆየው ኢህአዴግ መራሹ መንግስት በአደባባይ ለሰራው ስህተት ሕዝቡን ይቅርታ ሳይጠይቅ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በሚል ማክበሩ ሲያስተቸው ቆይቷል። መንግስት ከምርጫ 97 በሁዋላ የባንዲራ፣የብሄር ብሄረሰቦች፣ የመከላከያ ቀኖች እያለ በመቶ ሚሊዮኖች የሞቀጠር ገንዘብ በማውጣት ያከብራል።

ባንዲራዉ ላይ የተለጠፈዉ ባዕድ አካል የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና ነጻነት መግለጫ ነዉ የሚለዉን የወያኔ ጩኸት አስመልክተን አዲስ አበባ ድረስ ስልክ ደዉልን የጠየቅናቸዉ አንድ የህግ ባመለሙያ ፤ ወያኔዎች ባንድራዉ ላይ የለጠፉት ከኮብ የብሄረሰቦቻችን እኩልነት መግለጫ ነዉ ብለዉ ከሚፏልሉ ለምን በተጨባጭ እያንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ የእነሱ አዛዥነትና የበላይነት ሳያስፈለግዉ እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር አያደርጉም? ደግሞስ ይህንን በአማራና በኦሮሞ ብሄረሰቦች ላይ የከፈቱትን ዘመቻ ለምን አያቆሙም ካሉ በኋላ ወያኔዎች እዉነትም ለህዝብ መብትን ነጻነት ቆመዉ ከሆነ አንደኛ ህዝብ የሚፈልገዉ አረንጓዴ፣ ብጫ፤ ቀይ ባንዲራዉን ነዉና የፍላጎቱን ያደርጉለት፤ ሁለተኛ የህዝብን የግልና የቡድን መብት ሙሉ ለሙሉ ያክብሩ ብለዋል።

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የፕሬዚዳንቱን

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ከአሁን አሁን መብራት መጥቶና ኔትወርኩ ተስተካክሎ አገልግሎት እናገኛለን ብለው ተኮልኩለው ሲጠብቁ ታገኛለህ። አንዳንዴ መብራቱ መጥቶ ኔትወርኩ እምቢ ካለ ቀኑን ሙሉ ተጎልተህ ውለህ ብር ሳታገኝ ወደቤትህ ልትሄድ ትችላለህ። ይህ ዓይነቱን ቀውስና ኪሳራ ምን ዓይነት ይቅርታ ይተካዋል" ሲሉ ጠይቀዋል። ሌላው አስተያየት ሰጪ ፕሬዚደንቱ በንግግራቸው የመብራት መቆራረጥ አንዱ ምክንያት የመልካም አስተዳደር ችግር ነው ማለታቸውን አስታውሶ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር ካለ ችግሩን መፍታት፤ ካልተቻለ ለሚችል ኃይል ስልጣን መልቀቅ እንጂ ዕድሜ ዘላለም ሰበብ እየደረደሩ ለመቀጠል መሞከር ሕዝብን መናቅ ነው ብለዋል።